መልእክት ሰባት

**ዳዊት ክርስቶስን፣ እውነተኛውን ዳዊት—**
**የሚመጣውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ንጉሥ—በምሳሌ ማሳየቱ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ 1 ሳሙ. 21፡1-6፤ 2 ሳሙ. 7፡16፤ 23፡1-7፤
አሞ. 9፡11-12፤ ማቴ. 1፡6፤ 12፡1-4

**I. ዳዊት ክርስቶስን፣ እውነተኛውን ዳዊት በምሳሌ ያሳያል—1 ሳሙ. 21፡1-6፤ 2 ሳሙ. 23፡1-7፤ ማቴ. 12፡1-4፦**

ሀ. ዳዊት ለረጅም ጊዜ የቆየ በብሉይ ኪዳን የተገለጠ የክርስቶስ ሙሉ እና ጥልቅ-ዝርዝር ምሳሌ ነው፤ አዲስ ኪዳንም ዳዊት ክርስቶስን በምሳሌ እንደሚያሳይ በግልጽ ይገልጣል—ማቴ. 12፡3።

ለ. በማቴዎስ 12 የሚታየውን ክርስቶስ ከምሳሌዎች ሁሉ የሚበልጡን፣ በብሉይ ኪዳን ካሉ እርሱን በምሳሌ ከሚያሳዩ ነገሮች እና ሰዎች ሁሉ የሚበልጡን መርህ በመከተል፣ ክርስቶስ የሚበልጠው ዳዊት ነው፦

1. በማቴዎስ 12፡3-4 ያለው የጌታ ቃል እርሱ እውነተኛው ዳዊት መሆኑን ያመለክታል፦

ሀ. ዳዊት ተከታዮች ነበሩት፣ ክርስቶስ፣ እውነተኛው ዳዊት ተከታዮቹ የሆኑ ደቀ መዛሙርት ነበሩት።

ለ. ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ዳዊት እና ተከታዮቹ የክርስቶስ እና የደቀ መዛሙርቱ ምሳሌ፣ ቅድመ ስእል፣ እንደሆኑ ነው።

2. በማቴዎስ 12፡3-4 ያለው የጌታ ቃል ከክህንነት ወደ ንግሥና የሆነውን መግቦተ ዘመናዊ ለውጥንም ጭምር ያመለክታል፦

ሀ. የዳዊት መምጣት መግቦተ ዘመኑን ነገሥታት ከካህናት በላይ ወደ ሆኑበት ከካህናት ዘመን ወደ ነገሥታት ዘመን ለወጠው።

ለ. በክርስቶስ መምጣት፣ መግቦተ ዘመኑም ተለወጠ፣ በዚህ ጊዜ ክርስቶስ ከሁሉ በላይ ወደሆነበት ከሕግ ዘመን ወደ ጸጋ ዘመን።

ሐ. በማቴዎስ 1፡6 ዳዊት "ንጉሥ" ተብሏል ምክንያቱም መንግሥቱ ከንግሥናው ጋር የመጣው በእርሱ በኩል ስለነበረ ነው፤ እርሱ የሁለት ዘመናት ዋና፣ የአንድ ዘመን መደምደሚያ እና የሌላ ዘመን መጀመሪያ ነበር።

ሐ. ዳዊት መከራ የሚቀበለውን ክርስቶስ በምሳሌ ማሳየቱ በመዝሙር 22፣ 109 እና 110 ተገልጧል፦

1. በመዝሙር 22 መከራ የሚቀበለውን ክርስቶስ በምሳሌ የሚያሳየውን በሞቱ በኩል በማለፍ መከራ የሚቀበለውን ዳዊት እናያለን—ቁ. 1፣ 6-21።

2. መዝሙር 109 መከራዎቹን በተመለከተ በዳዊት የቀረበ ጸሎት ነው፦

ሀ. እዚህ ጋር ዳዊት የክርስቶስ ምሳሌ ነው፣ የዳዊት መከራዎች የክርስቶስን መከራዎች በምሳሌ ያሳያሉ።

ለ. መከራዎቹን በተመለከተ የዳዊት ጸሎት የክርስቶስን ጸሎት በምሳሌ ያሳያል።

3. በመዝሙር 109 ያለው ጸሎት በመዝሙር 110 ተመልሷል፦

ሀ. መዝሙር 110 ለዳዊት ጸሎት መልስ ስለሆነ በመዝሙር 109 እንዳለ የክርስቶስ ምሳሌ መዝሙር 110 የክርስቶስ ጸሎት መልስ ተደርጎ መቆጠር አለበት—ዕብ. 5፡7።

ለ. እግዚአብሔር ይህንን ጸሎት የመለሰው በክርስቶስ ትንሣኤ በኩል ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ዕርገት በኩልም ጭምር ነው—ሐዋ. 2፡23-24፣ 32-33፤ 5፡31።

መ. ዳዊት በመጨረሻ ቃሎቹ ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል—2 ሳሙ. 23፡1-7፦

1. የክርስቶስ ምሳሌ የሆነው ዳዊት በሰዎች መካከል በእግዚአብሔር ፍርሃት በጽድቅ ገዛ—ቁ. 3።

2. የክርስቶስ ምሳሌ የሆነው ዳዊት ፀሐይ ያለ ደመና ስትወጣ እንደሆነ እንደ ማለዳ ብርሃን ነበር—ቁ. 4።

3. ክርስቶስ በሰዎች መካከል በእግዚአብሔር ፍርሃት በጸድቅ ሲገዛ፣ ፀሐይ ስትወጣ እንደሆነ እንደ ማለዳ ብርሃን፣ "ከዝናብ በኋላ ከምድር እንደሚበቅል ልምላሜ ይሆናል"—ቁ. 4።

**II. ንጉሡ ዳዊት ንጉሡን ክርስቶስ በምሳሌ ያሳያል—1 ሳሙ. 16፡12፤ 2 ሳሙ. 16፡5-6፤ ማቴ. 1፡6፤ 2፡2፤ 27፡11፤ ራእ. 19፡16፦**

ሀ. ንጉሥ ዳዊት በእግዚአብሔር እንደተሾመ፣ እንደ ተዋጊው ንጉሥ፣ እና በሰዎች እንደተናቀ እና ሰዎች እንዳልተቀበሉት ንጉሥ ክርስቶስን—የሚመጣውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ንጉሥ—በምሳሌ ያሳያል—1 ሳሙ. 16፡12፤ 2 ሳሙ. 16፡5-6፦

1. በዳዊት እንደተመሰለው፣ በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ድል የተቀዳጀው፣ ምድሪቱን የራሱ ያደረገው፣ እና እንደ እግዚአብሔር መቅደስ ለቤተ ክርስቲያን መገንባት ግብዓቶቹን ሁሉ ያዘጋጀው ክርስቶስ ተዋጊው ንጉሥ ነው—1 ዜና 21፡22-25፤ 29፡29።
2. ክርስቶስ ምድርን የራሱ ካደረገ በኋላ፣ በመንግሥቱ ውስጥ እንደ ንጉሥ ከድል ነሺ አማኞቹ ጋር በአሕዛብ ላይ በመግዛት በምድር ላይ ይገዛል—ራእ. 20፡4፣ 6፤ 2፡26-27።
3. እንደሚመጣው ንጉሥ ክርስቶስ በሺው ዓመት የሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ራስ እና ማዕከል ይሆናል፤ ይህ የኢሳይያስ 32፡1፣ የኤርሚያስ 23፡5፣ እና የዘካርያስ 14፡9 እና 17 መፈጸም ይሆናል።

ለ. ነቢያት ዳዊት እና ክርስቶስ አንድ ስለመሆናቸው ተናገሩ—ኤር. 30፡9፤ ሕዝ. 34፡23-24፤ 37፡24-25፤ ሆሴ. 3፡5፤ አሞ. 9፡11፦

1. "ለአምላካቸው ለእግዚአብሔርም ለማስነሣላቸው ለንጉሣቸው ለዳዊትም ይገዛሉ"—ኤር. 30፡9።
2. ይህ እውነተኛው ዳዊት የሆነውን እና በመታደስ ጊዜ፣ ማለትም፣ በሺው ዓመት ንጉሥ የሚሆነውን ክርስቶስን ያመለክታል—ኢሳ. 32፡1፤ ራእ. 20፡4፣ 6።
3. "በላያቸውም አንድ እረኛ አቆማለሁ እርሱም ያሰማራቸዋል፥ እርሱም ባሪያዬ ዳዊት ነው፤ ያሰማራቸዋል እረኛም ይሆናቸዋል። እኔም እግዚአብሔር አምላክ እሆናቸዋለሁ ባሪያዬም ዳዊት በመካከላቸው አለቃ ይሆናል"—ሕዝ. 34፡23-24፦

    ሀ. ዳዊት እኛን የሚመግበንን እና እንድንሞላ እና እንድንረካ የሚያደርገንን እውነተኛው የእግዚአብሔር መንጋ እረኛ የሆነውን ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል—ዮሐ. 10፡11፤ ዕብ. 13፡20፤ ኢሳ. 9፡7፤ ሆሴ. 3፡5፤ ሚክ. 5፡2፤ ሉቃ. 1፡32-33።

    ለ. ጌታ ኢየሱስ እንደ እረኛ እኛን ለመንከባከብ ሲመጣ፣ እኛን ለመግዛት እንደ ንጉሥም ጭምር ይመጣል፤ ጌታ እንደ እረኛችን እኛን የመንከባከቡ ውጤት እንደ ንጉሣችን እርሱን መታዘዛችን እና በውስጣችን ካለው ከንግሥናው እና ከዙፋኑ ሥር መሆናችን ነው።

4. "ባሪያዬም ዳዊት ንጉሥ ይሆናቸዋል፤ ለሁሉም አንድ እረኛ ይሆንላቸዋል"—ሕዝ. 37፡24፦

    ሀ. ይህ እውነተኛው ዳዊት የሆነውን ክርስቶስን እንደ እረኛችን ያመለክታል።

    ለ. ከእስራኤል ጋር በተገናኘ እዚህ ጋር የተሰጠው ትንቢት በሺው ዓመት፣ በመታደስ ዘመን፣ እና በዘላለም፣ በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር ይፈጸማል።

5. "ከዚያም በኋላ የእስራኤል ልጆች ተመልሰው አምላካቸውን እግዚአብሔርንና ንጉሣቸውን ዳዊትን ይፈልጋሉ፤ በኋለኛውም ዘመን ፈርተው ወደ እግዚአብሔርና ወደ በረከቱ ይመጣሉ"—ሆሴ. 3፡5፦

    ሀ. ንጉሣቸው ዳዊት ክርስቶስ በሺው ዓመት ነው።

    ለ. *ኃለኛው ዘመን* የመታደስን ዘመን ያመለክታል—ማቴ. 19፡28።

ሐ. በመጪው የጌታ ንግሥና የእግዚአብሔር ሥልጣን እና ክብር በሙላት ይገለጣል፣ መላው ምድርም ከሕዝቧ ጋር ወደ ጽድቅ፣ ሰላም፣ ደስታ እና ወደ እግዚአብሔር ፍጥረት ሙሉ በረከት ይመጣሉ—6፡13፤ ኢሳ. 32፡1፣ 16-18፤ 35፡1-2፣ 5-7።

## III. የዳዊት መንግሥት የሚመጣውን የክርስቶስ መንግሥት በምሳሌ ያሳያል—2 ሳሙ. 7፡12፣ 16፤ ማር. 11፡10፤ ራእ. 11፡15፦

ሀ. በነቢዩ ናታን በኩል፣ ያህዌ ለዳዊት እንዲህ ሲል ተናገረ "ቤትህና መንግሥትህም በፊቴ ለዘላለም ይጠነክራል፥ ዙፋንህም ለዘላለም ይጸናል"—2 ሳሙ. 7፡16፦

1. የዳዊት ቤት ክርስቶስን ያመለክታል፣ የዳዊት መንግሥት የክርስቶስን መንግሥት ያመለክታል፣ የዳዊት ዙፋን የክርስቶስን ዙፋን ያመለክታል—ቁ. 16።
2. የዳዊት መንግሥት የክርስቶስ መንግሥት ነው፣ ዳዊት እና ክርስቶስ አንድ ዙፋን አላቸው—ኢሳ. 9፡7፤ 16፡5፤ ሉቃ. 1፡32፤ ሐዋ. 2፡29-31።
3. የመላእክት አለቃ በሆነው ገብርኤል የተላለፈው የእግዚአብሔር ቃልም ጭምር የዳዊት ቃል ኪዳን በክርስቶስ እንደሚፈጸም አረጋግጧል—ሉቃ. 1፡32-33።
4. የዳዊት ቤት እና መንግሥት እንደሚጠነክር እና ዙፋኑ ለዘላለም እንደሚጸና እግዚአብሔር ለዳዊት የገባው ቃል ኪዳን በክርስቶስ ተፈጽሟል።
5. በያዕቆብ ቤት ላይ ለዘላለም እንዲነግሥ እና ለመንግሥቱ መጨረሻ እንደማይኖረው እግዚአብሔር ለዳዊት በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ክርስቶስ የዳዊትን ዙፋን ይወርሳል—ቁ. 32-33፦

ሀ. በሚመጣው ዘመን የሺው ዓመት መንግሥት ምድራዊው ክፍል በማቴዎስ 13፡41 የሰው ልጅ መንግሥት ተብሎ የተጠራው የመሲሁ መንግሥት ይሆናል (ራእ. 11፡15)።

ለ. ይህ የታደሰው የእስራኤል መንግሥት (ሐዋ. 1፡6)፣ ጌታ እንደገና የሚሠራት የዳዊት ድንኳን—የዳዊት መንግሥት—ይሆናል (15፡16፤ ማር. 11፡10)።

ሰ. ክርስቶስ እንደ ንጉሥ "የወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን" እንደሚያነሣ አሞጽ ተንብዮአል—አሞ. 9፡11፦

1. የዳዊት ድንኳን የዳዊት መንግሥት እና የዳዊት ንጉሣዊ ቤተሰብ ነው—2 ሳሙ. 7፡12፣ 16።
2. ያ መንግሥት፣ ያ ንጉሣዊ ቤተሰብ የወደቀው ናቡከደነፆር የእስራኤልን ሕዝብ ለመማረክ፣ ምድሪቱን ለማውደም፣ ከተማይቱን ለማቃጠል፣ መቅደሱን ለማጥፋት እና ንጉሡን ለመውሰድ በመጣ ጊዜ ነው—2 ነገ. 25፡1-21።
3. የሆነ ቀን የዳዊት መንግሥት እና የዳዊት ቤተሰብ እንደሚመለስ እና አሕዛብም ሁሉ በያህዌ ስም እንደሚጠሩ በአሞጽ ትንቢት እግዚአብሔር ቃል ገብቷል—አሞ. 9፡11-12።
4. ይህ ትንቢት ክርስቶስ እውነተኛው ዳዊት ለመሆን ተመልሶ እንደሚመጣ (ኢሳ. 9፡7፤ 16፡5፤ ኤር. 30፡9፤ ሕዝ. 34፡23-24፤ 37፡24-25፤ ሆሴ. 3፡5) እና ለመላው አጽናፍ-ዓለም መታደስ የአባቱን የዳዊት መንግሥት እንደገና እንደሚሠራ፣ ማለትም፣ እንደሚያድስ ያመለክታል።
5. በዚያን ጊዜ የዳዊት መንግሥት ለዘላለም የክርስቶስ እና የእግዚአብሔር መንግሥት ትሆናለች—ራእ. 11፡15።
6. ጌታ በዳዊት ዙፋን ላይ ይቀመጣል፣ በያዕቆብ፣ ማለትም፣ በአይሁድ ሕዝብ ላይም ይነግሣል (ሉቃ. 1፡32-33)፣ በሺው ዓመት ጊዜ በምድር ላይ ባሉ በአሕዛብም ላይ ይገዛል (መዝ. 2፡8፤ 72፡8፤ ዳን. 7፡14፤ 2፡35)።

*© 2021 Living Stream Ministry*